በአገራዊ የሠላም ስምምነቱ ላይ  የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

ጥቅምት 26፣ ቀን 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በአገራችን ኢትዮጵያ ለሁለት ዓመታት የዘለቀውን ግጭት  በሰላም ለመፍታት ጥቅምት 23 ቀን፣ 2015 ዓ.ም በመንግሥትና በህወሓት መካከል ደቡብ አፍሪካ ላይ የተደረገውን የሰላም ስምምነት በከፍተኛ ደስታ እና በታላቅ ተስፋ ተቀብለነዋል።

በሴቶች መብቶች ላይ የሚሠሩ ሲቪክ ተቋማት የውይይትና የትብብር መድረክ የሆነው 'ጀንደር ኢን ፎከስ'፣ የ 35 ሴቶች ማኅበራት ስብስብ ከሆነው የኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበራት ቅንጅት (ኢሴማቅ) ጋር በመሆን የተጀመረው የሰላም እርምጃን በእጅጉ የምናደንቅ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን።

ይህ የሰላም ስምምነት እንዲደረግ መግባባት ላይ የደረሱትን መንግሥትና ህወሓትን፣ ለስምምነቱ እውን መሆን ከፍተኛ ሚና የተጫወተው የአፍሪካ ሕብረትንና ዓለምአቀፉን ማህበረሰብ እናመሰግናለን።

ይህ ጦርነት ከተጀመረ ጀምሮ በተለያዩ መንገዶች ግጭቱ እንዲቆም ተከታታይ ውትወታ እና አልፎም ለተጎጂዎች ሰብዓዊ እርዳታዎች እንዲደርሱ የበኩላችንን ስናድርግ ቆይተናል።

ማንኛውም ግጭት በተለይም በሴቶችና ሕፃናት ላይ የተለየ ጉዳት እንደሚያስከትል ይታወቃል። ለዚህም ይህ የሰላም ስምምነት ለእኛ ከታች ስማችን የተጠቀሰው በሴቶች መብት ዙሪያ ለምንሠራ ድርጅቶች የተለየ ደስታ እና ተስፋ የሚሰጥ ነው።

ግጭቱ እንዲቆምና ተጎጅዎች ድጋፍ እንዲያገኙ  የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርግ የነበረው  'ጀንደር ኢን ፎከስ' ከዚህ በኋላም ጥረቱን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ያረጋግጣል።

ከዚህ ቀደምም የተለያዩ ጥረቶችን ስናደርግ እንደቆየነው ፣ አሁንም  ለዚህ ሰላም ስምምነት ዘላቂነትና ውጤታማነት መረጋገጥ የበኩላችንን ጥረት የምናደርግ መሆኑን የዚህ መድረክ አባላት እንገልፃለን።